28ኛ ዓመት አዋጅ ቁጥር 178
አሶሳ ሀምሌ 2013

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

# ልሣነ-ሕግ ጋዜጣ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትን እንደገና ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 149/2009 አንቀጽ 18ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የክልሉ ውሃ ስራዎችና ኮንስትራክሽን ድርጂት እየገነባቸው ካሉት ከፍተኛ የውሃ ተቋማትና ህንጻ ስራዎች በተጨማሪ ከፍተኛ የመስኖ ግንባታዎች እንዲያካሂድ ስለተፈለገ እና እነዚህን ስራዎች ለመፈጸም የድርጂቱን አቅም በማጎልበት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ በመሆን ጥራቱን የጠበቀ ስረዎችን እንዲሰራ ለማስቻል የመበደር አቅሙን ከፍ ማድረግ በማስፈለጉ በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 49(3.1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሥራዎች እናኮንስትራክሽን ድርጅትን እንደገና ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 149/2009 አንቀጽ 18ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 178 /2013 “ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ማሻሻያ

የአዋጁ አንቀጽ 18 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 18 ተተክቷል፡፡

አንቀጽ 18

## <u>የተጠያቂነት ወሰን</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ መበደር ከፈለገ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሰት እና የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ኃላፊነት እዲወስድ ያደረጋል፡፡

## <u>አንቀጽ 3</u>

## <u>አወጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሐምሌ 16/ 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

አሻድሊ ሀሰን አልአጅብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ኘሬዚዳንት